ጸጋ መምህርም ነው!

የእግዚአብሔር ጸጋ ኃጢአተኞችን በነፃ ሊያጸድቀን የተገለጠ የጌታ ስጦታ ነው **(ሮሜ 3፡21-24)**። የእግዚአብሔር ጸጋ በደለኞችን ከጥፋት ሊያድነን የወረደ መለኮታዊ አሠራር ነው **(ኤፌ 2፡1-5፣ 8-9)**። የእግዚአብሔር ጸጋ ሙታኖቹን ሕይወት ሊሰጠን የፈሰሰ የፈጣሪ ልግስና ነው **(ሮሜ 6፡23፣ ኤፌ 2፡4-5)**።

የእግዚአብሔር ጸጋ ሊያጸድቀን መገለጡን ብዙዎች ተረድተናል፣ ሊያድነን መውረዱን አያሌዎች አውቀናል፣ ሕይወት ሊሆነን መፍሰሱን በርካቶች ተገንዝበናል። ለመሆኑ ግን ይህ መለኮታዊ ጸጋ ሊያስተምረን መምጣቱን የምናውቅስ ስንቶቻችን ነን?? ጸጋው ከኃጢአት ርቀን በቅድስና እየተመላለስን ጌታን በተስፋ እንድንጠብቅ የሚነግረን መምህራችን እንደሆነስ የተረዳን ምን ያህሎቻችን ነን??

ብዙዎች የጸጋን ትምህርት ሲተቹ ይደመጣል። ለኃጢአት ፈቃድ የሚሰጥ ትምህርት እንደ ሆነ ሲናገሩም ይስተዋላል። ጸረ ቅድስና ሲሉም ይጠሩታል። ሆኖም የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረው በተቃራኒው ነው። ጸጋው ሊያጸድቀን የመውረዱን ያህል፣ ሊያድነን የመገለጡን ያህል፣ ሕይወት ሊሆነን የመፍሰሱን ያህል ከኃጢአት የራቀ የቅድስና ሕይወት እንዲኖረንም ያስተምረናል። እንዲህ ተብሎ እንደ ተፃፈ፡-

"**11**፤ ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና። **11-13**፤ ይህም ጸጋ፣ ኃጢአተኝነትንና ዓለማዊ ምኞትን ክደን የተባረከውን ተስፋችንን እርሱም የታላቁን የአምላካችንንና የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር መገለጥ እየጠበቅን፣ ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ እግዚአብሔርንም በመምሰል በአሁኑ ዘመን እንድንኖር ያስተምረናል።" **(ቲቶ 2፡11-13)**

ጸጋ ኃጢአትን የሚጨምር፣ ቅድስናን የሚያጠፋ አይደለም። ይህንን የሚያደርገው ጸጋ ሳይሆን ሕግ ነው። መጽሐፍ "በደልም እንዲበዛ ሕግ ጨምር ገባ፤ ..." እንዲል ሕግ የተሰጠው ኃጢአት እንዲታወቅ፣ በደል እንዲበዛ ነው **(ሮሜ 3፡20፣ 5፡21)**። ጸጋ ኃጢአትን እንደሚያስፋፋ የሚገልጹ ወገኖች ኃጢአትን ለመቀነስ ሕግን መፍትሄ ሲያደርጉ ይስተዋላል። ሆኖም የእግዚአብሔር ቃል ሕግ ኃጢአትን ለመጨመር፣ ጸጋ ደግሞ ቅድስናን ለማስተማር መግባታቸውን ይነግረናል። ስለዚህ የጸጋን አስተምህሮ የመቃወም ዝንባሌ የሚመነጨው ከሕግ ጋር ያለውን ልዩነት በአግባቡ ካለመረዳት ነው ማለት ነው።

ጸጋ የፈሰሰው ቅድስናን ለመግለጥ እንጂ ኃጢአትን ለመጨመር አይደለም። ጸጋ የወረደው ከሰው ላይ ቅድስናን ለማጥፋት አይደለም፤ ጠፍቶ የነበረው ቅድስና ላይ ሕይወት ለመዝራት እንጂ። ጸጋ ከመገለጡ በፊት ሰው ኃጢአተኛ ብቻ ሳይሆን የኃጢአት ባሪያም ጭምር ነበር **(ሮሜ 6፡17-18)**። ሆኖም መጽሐፍ "በነፃነት ልንኖር ክርስቶስ ነፃነት አወጣን" እንዲለን እግዚአብሔር በልጁ ሞት በኩል ባፈሰሰው ጸጋ ከኃጢአት ነፃ ወጣን **(ገላ 5፡1)**።

አንዳንዶች ጸጋ ለኃጢአት ነፃነት የሚሰጥ ቢመስላቸውም እውነታው ግን ጸጋ ከኃጢአት ነፃነት የሚሰጥ ነው። ብዙዎች ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት መኖር እንደሚያስፈልግ ቢያስቡም ሀቁ ግን ጸጋው የበዛው በኃጢአት ከመኖር ሊያላቅቀን ነው **(ሮሜ 3፡8፣ 6፡17-18)**። ጸጋን በተመለከተ በሰዎች ዘንድ

የሚስተዋለው እንዲህ ያለው የተሳሳተ አመለካከት በእኛ ጊዜ የጀመረ አይደለም። በሐዋርያው ጳውሎስ ዘመንም የነበረና እንዲህ ሲል መልስ የሰጠበት ጉዳይ እንጂ፡-

"እንግዲህ ምን እንላለን፣ ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም። ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?" **(ሮሜ 6፡1-2)**

በክርስቶስ ሞት በኩል የፈሰሰው መለኮታዊ ጸጋ ኃጢአት ውስጥ ተነክረን ለነበርነው ሰዎች ነፃ አውጪ ሆኖ ተገልጦአል። ኃጢአታችን በዝቶ ለነበርነው ሰዎች የእግዚአብሔር ጸጋ ከዛ ይልቅ በዛ፤ ነፃም ወጣን። በደላችን ጨምሮ ለነበርነው ሰዎች የአምላክ ጸጋ ከመጠን በለጠ፤ አርነትም አገኘን **(ሮሜ 5፡20-21)**። ይህ ነው የጸጋ እውነት።

ጸጋ ኃጢአትን ሊያበዛ ሳይሆን ሊያስወግደው ወርዶአል። ጸጋ ቅድስናን ሊያጠፋ ሳይሆን ሊገልጠው ፈሷል። ከኃጢአት የተላቀቀን የቅድስና ሕይወት መኖር ለሚሻ ጸጋ መፍትሄ ነው። ለዚህ ደግሞ የጸጋ አማኞች የሆንን እኛ ሕያዋን ምስክሮች ልንሆን ይገባል። ከነበርንበት እርኩሰት አላቆ ቅድስናን እንድንገልጥ ምክንያት የሆነን ሌላ ሳይሆን የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ሆነ ሕይወታችን መመስከር አለበት። ጸጋ ኃጢአትን ለማድረግ ነፃ እንደሚያወጣ ለሚሰማው ስሁት አመለካከትም ጸጋ ኃጢአት ከማድረግ እንጂ ለማድረግ አርነት እንደማያወጣ በሕይወት ማሳየትና የጸጋን ትምህርት ማስከበር ከእኛ ይጠበቃል።

ጸጋ ነፃ ያወጣን በኃጢአት ከመኖር እንጂ በኃጢአት ለመኖር አይደለም!!

ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን

ቢኒያም በርሄ

የ "ከበፊት እስከ ወደፊት" መጽሐፍ ጸሀፊ

ነሀሴ 23/ 2014